# መብትን በተመለከተ ማስረጃ መፅሄት

## እስከ 18 ዓመት ለሆኑ ወጣቶች

### የስኳር በሽታ (ኣይነት 1) ታማሚ

### የእስራኤል ማህበር

JDRF

IMPROVING LIVES. CURING TYPE 1 DIABETES.

## መግቢያ

ይህን መፅሄት የፃፍነው አላማችን ለእናንተ መብትን በተመለከተ የተለያዩ ማስረጃወች ለመዘከርና መብትን እንዴት በእግባቡ መጠቀም እንደሚቻል ለማስረዳት ነው።

ድርጊታችን የምንፈፅመው አዲስ ገቢወች የሚያስፈልጓቸውን አሳሳቢ ነገሮች በመመልከት ለመርዳት ስለሆነ ፤ እናንተም አስተያየታቹህን ብትገልፁልን እንወዳለን።

አተያዬት ፥ ጥያቄ ወይም የተለያዩ ሃሳቦች ካላቹህ በስልክ ቁጥር 03-516171 ወይም በኢንተርኔት ፎርማችን http://www.jdrf.org.il ልትገልፁልን ትችላላቹህ።

የስኳር በሽታ (ኣይነት 1) ታማሚ የእስራኤል ማህበር አላማ ለሁሉም ዕድሜ ስኳር በሽታ ለተያዙት (አይነት 1) ወግኖቻችን ፥ በህዝባዊና መንግስታዊ አባላቶች ፊት በመቆም መብታቸዉን በመጠበቅ አሳሳቢና አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች በማሟላት የተሻለ ኑሮ እንዲኖራቸው ይሆናል።

ይህ መፅሄት በሃኪም ቤት ፥ የጤና ጥበቃ ሚንስቴር ፥ የጦረታ አባልና የውትድርና አገልጋዮች ወዘተ... ለመሳሰሉት ቦታወች ከ-18 ዓመት በላይ ልሆኑ ግለሰቦች ምን አይነት መብት እንዳላቸው ያብራራል።

በተጨማሪም በመፅሄቱ ውስጥ ከሚያስፈልጉ ቦታወችና ቅርንጫፎች ለመድረስ የተለያዩ ምንገዶች በመጠቆና አስፈላጊ የሆኑ ዶክሜንቶች በድረ ገፃችን የማውረድ አገልግሎት ይሰጣል።

የድረ ገፃችን አድራሻች - http://www.jdrf.org.il

JDRF IMPROVING LIVES. CURING TYPE 1 DIABETES.
האגודה לסוכרת נעורים (סוג 1) בישראל

## በእስራኤል ስለ የወጣቶች ስኳር በሽታ (ዓይነት 1) ምርመራ ፋውንዴሽን።

በእስራኤል የወጣቶች ስኳር በሽታ ብሄራዊ ድርጅት የተቋቋመው ልጃቸው በስኳር በሽታ የተመመባቸው ወላጆች በ-1983 ዓ.ም ሲሆን በዛሬው ዕለት ደግሞ ለሁሉም ህዝብ የሚያገለግል ድርጅት ነው። የማህበር ድርጅቱ የዓለም አቀፍ እስራኤላዊያን ቅርንጫፍ ነው።

JDRF (Juvenile Diabetes Research Foundation) ዋና ድርጅቱ አሜሪካ ውስጥ ይገኛል።

የማህበሩ ሁለት ዋና ዋና ዓላማዎች

- ለስኳር በሽታ ፈዋሽ መድሃኒት ለማገኘት መጣጣርና ምርመራውን መከታተል።
- በሽታዉን የሚፈውስ መድሃኒት እስኪገኝ ድረስ የተጠበቀ ምርመራ በአግባቡ እንዲረዱ መደገፍ።

ኑሮና ህይወታቸዉን ለማሻሻልና ለማመቻቸት ማህበሩ በለያዩ መንገዶች መካከል እየተሳተፈ ይገኛል ፤ የሚያስፈልጉና አዳዲስ የቴክኖሎጂ መሰሪያወችን በማቅረብ ፤ የተለያዩ ማስረጃወችን በማቅረብ ፤ የስኳር በሽተኞችን መብት በመጠበቅ ፤ ለሁሉ የእስራኤልውያን ህዝብ ስለበሽታ አብራሪና ሰፊ ማስረጃ መዘከር ፤ ለስኳር በሽታ ታማሚወች ቅጥል ድጋፍ መስጠትና ስለበሽታዉ ምርመራ ለሚያደርጉ አባላቶች የገንዝንብ ድጋፍ እንሰጣለን።

ከዋናዋቹ የማህበራችን ግንባታ ከስኳር በሽታ ታማሚወች ጋር ሙሉ በሙሉ መጋራት ነዉ። የማህበራችን ብዛት ከብዙ ሺ የሚበልጡ ሲሆኑ ከቀን ወደ ቀን የሚረዱን በሁሉም እድሜ የሆኑ በጎ አድራጊ ግለሰቦች ናቸው። እኒህ በጎ አድራጊ ግለሰቦችም ማገዝ በአላቸው ፍላጎትና በታታሪ ስራቸው መሰረት ብዙወች ተሸልመዋል። በ 2004 ዓ.ም የፕሬዝዳንት ሽልማት ፤ በ 2015 ዓ.ም የበጎ አድራጊ ሽልማት። ከዛሬ 4 አመት በፊት መህበራችን "የካራክተር ውጤታማነት" ሽልማት በመሸልሙ ከተለያዩ ትላልቅ ድርጅቶች ጋር በመዘነቅ ለህብረተሰቡ ምናግዝውና ምንደግፈው ተስፋፍቷል።

## የማህበሩ ግኙት/ውጤት

- የበጋ ካምፖች ተክል ማቋቋም - ከ 10-18 ዓመት ለሆኑት ልጆች ካምፕ። በካምፑ የሚያገለግሉት ሰሪወች እራሳቸው የስኳር በሽታ ታማሚወች በመሆናቸው እስራኤል ባሉት ሁሉም ሀኪም ቤት አገልጋዮች ጋር ድጋፍ ይሰጣሉ።

- ለስኳር በሽታ ታማሚ (ዓይነት 1) ልጆ ክሊኒክ መክፈት።

- ለበሽታው የሚያገለግሉ መሳሪያወች ለ 3 ዓመት ያክል መስጠት።

- በሀገራችን 16 የህፃናት ሀኪም ቤቶች የ HbA1c መመርመሪያ መሰሪያወች መግዣ የገንዘብ እርዳታ መስጠት።

- በትምህርት ቤትና በትምህርት ሚንስቴር አባላት የእነዚህ ህፃናቶችን መብት መጠበቅ።

- ለእነዚህ ልጆች መቀበል የአለባቸውን የገንዘብ እርዳ እንዲደርሳቸዉ አባል ብሔራዊ ዋስትና ደንብ መቆም።

- ማህበራዊ የጤና ጉዳይ ጥበቃ ሚንስቴር ፥ የትምህርት ሚንስቴርና የመንግስት ድጋፍ ማገኘት።

- ኢንሱሊን ዕፅ ቅርጫት ማስገባት።

- አዳዲስ ኢንሱሊኖች ከዕፅ ቅርጫት ማስተላለፍ።

- እስከ 18 ዓመት ለሆናቸው የስኳር በሽታ (ዓይነት 1) ወጣቶችና ለአረገዙ እሴቶች የስኳር ብዛት መመርመሪያ መሳሪያ መስጠት።

- በሁሉም ሀኪም ቤቶች ለህክምና ምርመራ መሳሪያወች ክፍያ መወገድ።

- ለበሽታው መዳሃኒት ለማገኘት ለሚደርጉ መርማሪ አባላቶች የገንዘብ እርዳታ መዘከር። እስከዛሬ ከ 9 ሚልዮን ብር የሚበልጥ ገንዘብ ማህበራችን አስተላልፏል።

- ከ 3-9 ዓመት ለሁኑ ህፃናቶች እግዛት ማስረዘም።

- ውትድርና ለሚያገለግሉት በጎ አድራጊወች ኑሯቸዉን ማመቻቸት።

1. የስኳር በሽታ የህክምና አገልግሎት ፈቃደኛ ሠራተኞች መገለጫ ማሳደግ።

2. ከወታደሮች ዋና የጤና ሃላፊ ጋር የውትድርና አገልግሎታቸው ማመቻቸት።

- ለማህበርችን ቦርድ ማቋቋም።

• መረጃ የያዙ ስብሰባወች ለሁሉም ህብረተሰብ ማካሄድ።

• የስኳር በሽታ ታማሚችን ለማከም በሚፃፈው ዓለም አቀፍ ፕሮግራም ጋር መሳተፍ።

• ቅርንጫፍ ISF-JDRF፡ ከ JDRF ዋና ድርጅትና የእስራኤላውያን ዓልም አቀፍ ISF ድርጅት ጋር በመሳተፍ 1ኛ የስኳር በሽታ መርመሪ ማቋቋም። የቅርንጫፉ ገንዘብ 6 ሚልዮን ዶላር ነው።

• በእስራኤልና እንግሊዝ ሀገር በሚካሄደው አዳዲስ የተስፋፋ የህክምና ምርመራ BIRAX ፕሮግራም ጋር መሳተፍ።

• የካራክተር ውጤታማነት መጠኖች መቀበል።

## ዋና ዋና ተግባራት

• የበጋ ህክምና ካምፖች

• መብትን በማስጠበቅ የህይወት ጥራት ማሻሻል

• የኮንግሬስ ባለሞያ ድርጅት ማካሄድ

• ለኑሮችን ማሻሻያና ስለበሽታው መስፋፋት በቂ ማስረጃ ከድረገፃችን ታገኛላቹህ።• ሚዛናዊ “መፅሔት”

• ለህብረተሰቡ አዳዲስ ፕሮጄክቶች ማቋቋም።

• የስኳር በሽታ ብሔራዊ ምክር ቤት አማካኝነት በትዕግሥት እንክብካቤ መደበኛ ማስተዋወቅ

### ስለማህበራችን ለተጨማሪ ማብራሪያ፡

ድር ገፅ - www.jdrf.org.il

ኢሜ - office@jdrf.org.il

ስ.ቅ - 03-5160171

# ልጆቻቹህ የስኳር በሽታ ቢታመሙ ምን ማድረግ አለባቹህ?

## የስኳር በሽታ (ዓይነት 1) ምርመራ

የህክምና መብቶች
በዚህ መፅሔት የህክምና መብቶች ብሙሉ በዝርዝር ቀርበዋል። ሃኪም ቤታቹህ በመሄድ ብቁ መብት እንዳላቹህ ማረጋገጥ ይኖርባቹሃል።

ብሔራዊ ኢንሹራንስ

የጦረታ እርዳታ ለማገኘት ማረጋገጥ

ትምህርት ፕሮግራም ሚኒስቴር
ከትምህርት ቤት ሰራተኞች .1 ጋር ስብሰባና ስልጠና ማካሄድ
ለእርዳታ ጥያቄ ማቅረብ .2

ከ 6-18 ዓመት በወር የ 50% የገንዘብ እርዳታ መጠየቅ

ከ 0-6 ዓመት በወር የ 100% የገንዘብ እርዳታ መጠየቅ

ከ 3-9 ዓመት አካባቢያዊ ባለስልጣን በኩል የትምህርት ሚኒስቴር መጠየቅ

ከ 0-3 ዓመት የደህንነት ቢሮ አድራሻ መጠየቅ

በዕቅድ ተዛማጅ - ከጦረታ አባል የገንዘብ ድጋፍ ከተፈቀደላቹ በሥኋላ ከነዚህ ።ማስረጃወች መረዳት ታችላልቹህ።

ትላሊም - ትምህርት ቤት ስትመለሱ ዋና ማስረጃወች የአካል ችግር ላላቸው የገንዘብ እርዳታ

በአካባቢያዊ ባለስልጣ መሰረት የማዘጋጃ ግብር ቤት

በገቢ ግብር የግኝት ነጥቦች

ቤዜክ ድርጅት የቤት ስልክ መስመሮች

ብዙ የተለያዩ ቦታወች ስላሉ መብታቹህን በደምብ ማረጋገጥ የኖርባቹሃል።
መኖሪያ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚንስቴር፡ ቤት ለመግዛትና ለአፓርትመንት እድሳት ገንዘብ መበደር ይቻላል።
ዲኤምቪ (ምስራድ ሃሪሹይ)፡ የስኳር በሽታ ታማሚ ወላጆች ከክፍያ ነፃ ወይም የ 60% ቅናሽ ዋጋ ልትቀበሉ ትችላላቹህ።
የግብር ስልጣን፡ ከተሰበሰበ ገንዘብ መሳብ ወይም መውሰድ ከፈለጋቹህ ከግብር ክፍያ ትሆናላቹህ ፤ በተለይ ከ 70% በላይ በአካለ ጎደሎነት
የታወቁ። የገንዘብ ሚንስቴር፡ ቤት ለመግዛት ይግብር ቅናሽ ዋጋ ሊያገኙ ይችላሉ።

የህክምና መብት የሚሰጠው በዛሬው ጊዜ አኣስተያየት ሲሆን ከዚህ በታች በደምብ ይብራራሉ።

የስኳር በሽታ ሥር ሰደድ በሽታ እንደሆነ በሚታወቀው መሰረት መድሃኒትና ሌሎች የህክምና ቅርጫት በቅናሽ ዋጋ መግዛት ይችላሉ። ከዚህም በመቀጠል የህክምና ምርመራ መሳሪያወች በሃኪም ቤቶች አስተያይትና ፍቃድ ቅናሽ ዋጋ መቀበል ይቻላል።

በሽታው ሥር ሰደድ በሽታ መሆኑን ሃኪም ቤት ማስታወቅ ይኖርባቹሃል።

የስር ሰደድ በሽታ ታማሚ ደርብ (ለክፍያ) አስተሳሰብ

| የሃኪም ቤት ስም | ምዝገባ ክፍያ |
|---|---|
| ማካቢ | 881 ብር ለሶስት ወር (294 ብር ለወር) |
| ሃኪም ቤት | 921 ብር ለሶስት ወር (307 ብር ለወር) |
| ለኡሚ | 921 ብር ለሶስት ወር (307 ብር ለወር) |
| መኡሄዴት | 858 ብር ለሶስት ወር (286 ብር ለወር) |

## በደማችን የስኳርን ብዛት ማሰላሰያ መሳሪያ

የስኳርን ብዛት ማሰላሰያ መሳሪያ መግዛት ካለባቹህ ፥ ሃኪም ቤት በመሄድ ከዶክተር የመደሃኒት ማዘዣ ወረቀት መቀበል ይኖርባቹሃል። የእቃዉ ክፍያም በወጪው ክፍያ መጠን ይሆናል።

## ኢንሱሊን ፓምፕ

ከ-2000 ዓ.ም ጀምሮ በማህበራችንና በሌሎች ትግል ኢንሱሊን ፓምፕ በነፃ

እንዲታደል ተፈቅዷል።

ለመቀበል የተፈቀደላቸው

* የስኳር በሽታ hba1c 7.5 ደረጃ በላይ ታማሚ ለሆኑ
* የስኳር በሽታ በመታመማቸዉ በቀን 3 ጊዜ የኢንሱሊን መርፌ ለሚወጉ
* ደኬቶናዊነት ፥ ደም አሲዳዊነትና ዝቅተኛ የደም ስኳር ያለባቸው ታማሚወች

ይህን የህክምና መሳሪያ ለመቀበል ለተፈቀደላቸው በሙሉ ያሚያስፈልጉትን ቁሳቁሶች ትሚልተው ትረከባላቹህ ፥ ከተበላሸና ጉድለት ካለው ደግሞ በነፃ ለማሰራት ይችላሉ።

## በስኳር በሽታ ማሰላሰያ መሳሪያ የሚያልቁ ቁሳቁሶች

* ማክሸፊያ - ለራሳቹህ ብቻቹህን በማክሸፊያ መጠቀም ከፈለጋቹህ በነፃ መቀበል ትችላላቹህ
* መርፌ - ብቻቹህን ምርመራውን ለመከታተል ከፈለጋቹህ
* መርፌ ለመግዛት የ-90% ቅናሽ ዋጋ ትቀበላላቹህ።

የስኳር በሽታ መመርመሪይ ጨንገሮች መጋዛት ለሚፈልግ የ-10% ወይም 15 ብር መክፈል ይኖርበታል። ለተጨማሪ ማብራሪያ - http://bit.li/1YpjXRm

## ቅጥለታዊ የስኳር መለኪያ

ከ-2010 ዓ.ም ጀምሮ ማህበራችን ባደረገዉ እጥረትና ትግል መሰረት ሀሳባችን በጤና ጥበቃ ሚንስቴር በመቀበሉ ቅጥለታዊ የስኳር መለኪያ ፥ ስኳር በደማችን ውስጥ የበለጠ ውጤት ካሳዬ ማስጠንቀቂያ ምልክት የሚያሳይ መሳሪያ አስገብተናል።

ከ-18 ዓመት በታች ለሆኑ ወጣቶች የህክምና ፍቃድ ወረቀት በመቀበል የስኳር መለኪያ ይቀበላሉ።

እስከ 18 ዓምት ለሆኑ ወጣቶች የሚጠቅሙ ተዛማኞች

ይህን ቴክኖሎጂ መሰሪያ ከ-18 ዓመት በታች ለሆኑ የስኳር በሽታ (ዓይነት 1) ታማሚ ወጣቶች ሊያሰጥ የሚያስችል የወረቀት ምልክት ወይም ማስረጃ

1. ዕድሚያቸው ከ 8-18 የሆኑ ወጣቶች ቢያንስ 2 ጊዜ ከስኳር በሽታ ምክንያት የጭንቀት ጥቃት የደረሰበቸው
2. ዕድሚያቸው እስከ 8 ዓመት የሆኑና የሚዛን እጥረት ያጋጠማቸው

**የቴክኖሎጂ መሰሪያ የሚሰጠው ከስኳር በሽታ ሃኪም ቤት የማስረጃ ወረቀት የተቀበሉ ናቸው።

የሚጠቅሙ ተዛማቾች ዝርዝር

1. ዕድሚያቸው ከ 8-18 የሆኑ ወጣቶች ቢያንስ 2 የደም ማነስ አጋጣሚ

የደረሰበቸው (ቢያንስ የደም ማነስ ውጤቱ ከ 50 በታች ከሆነ) ፤ የምርመራው ውጤት በዋና የስኳር በሽታ መርማሪ ይረጋገጣል።

2. በ 6 ወር ውስጥ በሳምንት 4 ጊዜ ከ 70 በታች የደም ማነስ አጋጣሚ የደረሰባቸው አዕድሚያቸው እስከ 8 ዓመት የሆኑ ወጣቶች

በአምራቹ ድርጅት መምሪያ መሰረት በቴክሎኖጂ መሳሪያው ብዙ ቁሳቁሶችና እቃወች ስለሚያልቁና መቀየር ስላለባቸው ሙሉ በሙሉ መቀየር ይቻላል።

በ 2012 ዓ.ም የጤና ቅርንጫት አስተያየት መሰረት ተስፋፊና አዳዲስ ማስረጃወች ስለሚሰራጩ ከዚህ www.health.gov.il/hozer/mk01_2012.pdf ድረ ገፅ በመግባት መከታተል ይቻላል።

በ 2016 ዓ.ም አዳዲስና ለረጅም ጊዜ የሚያገለግሉ ኢንሱሊኖች በስኳር በሽታ ታማሚወች መዳሃኑት ቅርጫት በመግባቱ ፥ ከድርጅታችን ማብራራት ይቻላል።

## የሃኪም ቤት ጉብኝት ክፍያ ነፃነት

ጦረታ እና የአካል ጉዳት የገንዘብ እርዳታ ተቀባዮች ውስጣዊና ውጫዊ ሃኪም ቤት ጉብኝት ተቋማት ክፍያ ነፃነት አላቸው። የክፍያ ነፃነት መቀበል የሚቻለው በብሔራዊ ኢንሹራንስ አስተያየት ዝርዝር ነው።

## ለመጨረሻ

ከላይ በተቀሱት ማስረጃወች በሙሉ ጥያቄወች ካአላቹህና በመብታዊ መሰረት ጉዳት

ለደረሰባቹህ እርዳታ እንሰጣለን።

በተጭማሪም ሊረዷቹህ የሚችሉ የተለያዩ የስራ ባለሥልጣን ስላሉ ወደ እነሱ በመሄድ ማማከር ይቻላል።

የጤና ባለስልጣን ሚንስቴር ድህረ ገፅ (አታር ኢንተርኔት)

http://call.gov.il/infocenter/index?page=home

በእየከትመውና በሰፈራቹህ አካባቢ ባሉት ህኪም ቤቶችም ያሏቹህ ጥያቄወችን መጠየቅና ማማከር ትችላላቹህ። www.jdrf.org.il

ከእነዚህ ቦታወች እርዳታ ካአላገኛቹህ በቀጥታ አድራሻ "ርብቃ 29, እየሩሳሌም" ከሚገኘው ህጋዊ የጤና ጥበቃ ሚንስቴር አቤቱታ ሰሚ መስሪያ ቤት ጥያቂያቹህን መቅረብ ትችላላቹህ

ስ.ቁ *6800 l ፖስታ ቁ. 02-5655981

የኢሜል አድራሻ - kvilot@moh.health.gov.il

## ከማሕበራዊ የጦረታ አባል የወጣቶች መብት

ከ 18 ዓመት የሆኑ የስኳር በሽታ ታማሚ ወጣቶ ከብሔራዊ የጦረታ አባል የገንዝብ እርዳታ ይቀበላሉ። በማሕበራችን ተቋምና ከሌሎች ማሕበሮች ጋር በመጋራት የስኳር በሽታው (ዓይነት 1) መስፋፋቱን በተመለከተ የሚቀበሉት የገንዘብ እርዳታ ይወሰናል።

የገንዘብ እርዳታው በዕድሜ እድገት አስተሳሰብ ነው (በበሽታው መስፋፋት ወይም በህክምናው አመጣጠን አይደለም)።

ከ 0-6 ዓመት ህፃኖች 100% እርዳታ ይቀበላሉ።

ከ 6-18 ዓመት ልጆች 50% እርዳታ ይቀበላሉ።

ጭምር ገንዘብ የሚሰጠው በዕድሚያቸው አስተሳሰብ ስለሆነ ከኮሚቴው መሄድ አያስፈልግም። በሽታው በጣም ከጠነከረ የበለጠ ገንዘብ እርዳታ ለመቀበል የሚያስፈልጉትን ዶክሜንቶች በመሙላትና ወደ ኮሚቴው በመሄድ የተቃዉሞ ቃል ማሰማት ይቻላል።

ይሄን መፅሄት ስንፅፍና የገንዘብ እርዳትው እስከ 18 ዓመት እንዲሆን ብዙ ፍላጎትና ውይይት ስለምናደርግ ከድረ ገፅችን በመግባት መከታተል ይቻላል።

## የጥያቄ ማመልከቻ

* ከሚቀርባቹህ ብሔራዊ የጦረታ አባል በመሄድ ለመሙላት የሚያስፈልጉትን ዶክሜንቶች መቀበል ወይም ከድረ ገፃቸው ማውረድ ይቻላል።
* የተቃውሞ ቃል ማሰሚያ ማስረጃና ዶክሜንቶችን ከሚቀርባቹህ ብሔራዊ የጦረታ አባል በመሄድ ማቅረብ ይቻላል።

ማሳሰቢያ፥

የገንዘብ እርዳታው ካቆመበት ጀምሮ ስለሚሰጥ ዶክሜንቶችን በአግባቡ ተሎ በመሙላት ማቅረብ ይኖርባቹሃል።

* ስለልጁ የስኳር በሽታ መታመም ብሶቱ ሃኪም ቤት በመሄድ ተጨማሪ ማብራሪያ የተፈረመበት ማስረጃ መቀበል ይኖርባቹሃል።
* የተለያዩ አጋጣሚ ችግሮች ካሉ የህክምና ማስረጃ ወረቀት በማቅረብ ለኮሜት ውይይት ትጠራላቹህ።

## የማሕበራዊ ጦረታ አባል ህክምና ኮሚቴ

እስከ 12 ዓምት ለሆኑ ልጆች የገንዘብ ድጋፍ በፅድሜ አሰላሰል ስለሆነ ወደ ቦታው መሄድ አያስፈልግም።

- የጦረታ አባል ህክምና ኮሚቴ አላማ የበሽታውን መስፋፋት ፥ ምን ያክል አቅም እንደሚቀንስና ክስራ እንድሚወግድ በመመልከት ስንት ገንዘብ ለእርዳታ እንዲሰጥ ነው።
በኮሚቴው የአስተያየት ግብዣ በሽታው ምን ያክል ጉዳት እንዳደረሰባቹህ ፥ እንዴት ዓይነት ስራወች እንደሚያግዳቹህ ማብራራትና ማስረዳት ይኖርባቹሀል።
ኮሚቴው ለተጨማሪ ማብራሪያ ከጠራቹህ መገኘት ይኖርባቹሃል።
ኮሚቴው ተጨማሪ የህክምና ምርመራ ማድረግ ስለሚችል ዝግጁ ሁናቹህ መምጣት ይጠበቅባቹሀል።

## የቅድሚይ ዝግጅት

- የሚያስፈልጉትን ዶክሜንቶች በሙሉ በማሟላት በአስቀዳሚ ለጦረታ አባል ብትልኩና ለህክምና ኮሚቴ አሟልታቹህ ብታቀርቡ ይመረጣል።
- ዶክሜንቶች አስፈላጊ ጊዚያቸውን መጠበቅ ይኖርባቸዋል።
- በቃል ለማብራራትና ለመጨመር የምትፈልጉት ወረቀት ላይ ፅፋቹህ ብትመጡ ሊያግዛቹህ ይችላል።
- ልጦረታ አባል ህክምና ኮሚቴ ስትመጡ አብሯቹህ አንድ ሰው እንዲመጣ አስፈላጊ ነው።

## መቃወሚያ

የጥያቄው አለመሳካት መልስ ከተቀበላቹህ የተቃውሞ ማሰሚያ ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል።
የተቃውሞ ማሰሚይ ማስረጃውን ማቅረብ የሚቻለው ፍርድ ቤት ነው።
የተቃውሞ ማሰሚይ ማስረጃውን ለማቀረብ ከጦረታ አባል የፍርድ ቤት አማካሪ እርዳታ መቀበል ይቻላል።

በኮሚቴው መልስ መሰረት ስለ የአቅመ ዉሱን የገንዘብ ድጋፍና የእርዳታውን ጊዜ እርዝመት በተመለከተ የተቃውሞ ቃል ማሰማት ይቻላል።

## የውጭ እርዳታ አባላት

በሃይፋና ቤኤር ሼቫ ከተማ የሚገኙት “ያድ ምኩቬኔት” ተብለው የሚታወቁት አባላቶች በዶክሜንቱ አዘገጃጀት እርዳታ ይሰጣሉ ፤ እኒህን አባላቶች በስልክ ወይም ከቦታው በመሄድ ልታገኟቸው ትችላላቹህ።

አድራሻ
ሃፓሊም 16 ሃይፋ
ስልክ ቁጥር: 04-9126885
ፋክስ ቁጥር፡ 04-9126890
ኢሜል - merkazy@femi.com
ከእሁድ - ሀሙስ 08፡00-17፡00 ስዓት ቢሮው ክፍት ነው

ሚግዳል ኬኒዮን ሃኔጌቭ ኮማ 5, ያሜት ኤሊ ኮሄን, ቤኤር ሼቫ
ስልክ ቁጥር፡ 08-6831919
ፋክስ ቁጥር፡ 08-6831918
ኢሜል - yadm@mediton.co.il
ከእሁድ - ሀሙስ 08፡00-15፡00 እና እሁድ፥ ማክሰኞ፥ ሀሙስ 16:00-19:00 ስዓት ቢሮው ክፍት ነው
ድርጅት “ያዲድ” ተብሎ ከሚጠራው መብትን በተመለከተ አግልግሎ ሰጪ

האגודה לסוכרת נעורים (סוג 1) בישראל

በስልክ ቁጥር 1-700-500-313 እርዳታ መጠየቅ ይቻላል።

ከማሕበራዊ የጦረታ አባል የገንዘብ እርዳታ ለመቀበል ፍቃድ ታገኛቹህ በኋላ ከሌሎችም ተሚከተሉት ኩባንያ ድጋፍ ልታገኙ ስለምትችሉ ማረጋገጥ ይኖርባቹሃል።

* የከተማዊ ነዋሪወች ግብር - ከአካባቢያዊ ባለሥልጣን በመሄድ በንብረት ግብርና የውሃ ክፍያ ቅናሽ ዋጋ መጠየቅ ይችላሉ። ከዚህም በመቀጠል በሁሉም ከአካባቢያዊ ባለሥልጣን ድጋፋቸው የተለያየ ስለሆነ ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው።

* የግብር ክፍያ ማስተዋወቂያ ነጥቦች - ከማሕበራዊ የጦረታ አባል የገንዘብ እርዳታ ለተፈቀደላቸው ልጆች ፥ ከወላጆቹ አንዳቸው 2 የድጋፍ ነጥቦች ይቀበላሉ።

ለመሙላት የሚያስፈልጉት ዶክሜንቶች፡

ቅርፅ 116 - https://taxes.gov.il/TaxesFormsList/itc116a.pdf

ቅርፅ 127 - https://taxes.gov.il/TaxesFormsList/itc127.pdf

ከዚህ በተጨማሪ ልጁ የተቀበለውን የፍቃድ ማስረጃ ወረቀት አብራቹህ እንድታመጡ ያስፈልጋል።

ከአንድ ቤተሰብ 2 የጦረታ አባል እርዳታ የሚያገኙ ካሉ ቤተሰቦቻቸው እጥፍ (4) ነጥብ ያገኛሉ።

**ይህን የእርዳታ ወይም ድጋፍ ጥያቄ በየዓመቱ ማሳድስ ያስፈልጋል።

ለጆቻቸው የ 100% የገንዘብ ድጋፍ ሊሚቀበሉ ቤተስቦች የቤዜክ ኩባንያ ለቤት ስለክ የዋጋ ቅናሽ ይሰጣሉ።

## እርዳታና ድጋፍ የሚዘክሩ የተለያዩ ቦታወች

### የቤታቤት ሚንስቴር

*ቤት ለመግዛት ለሚፈልጉ ብድር መቀበል ይቻላል።

*ቤት ለማሳደስ እርዳታ ይሰጣሉ።

### የዲኤምቪ ሚንስቴር

60% የዋጋ ቅናሽ ይሰጣሉ

### የግብር ስልጣን

በአካል ጉዳትነት 70% የላቸው

### የገንዘብ ሚንስቴር

ቤት ለመግዛት ለሚፈልጉ የብድር ድጋፍ ያገኛሉ።

## የስኳር በሽታ (ዓይነት 1) ታማሚወች ትምህርት ተቋም

በሃካሚው ዶክተር ፍቃድ የስኳር በሽታ ታማሚወች መደበኛ ትምህርት ቤት ከተማሩ እንደ ሁሉም ተማሪወች በሁሉም ድርጊቶች ፥ ሽርሽር ፥ ጉብኝት ወዘተ... መሳተፍ ይችላሉ። ከዚህም በመቀጠል ትክክል የሆኑ የትምህርት ሚንስቴር አብራሪ ትዕዛዞች አሉ።

- የስኳር በሽታ ታማሚወች የጉልብትና ድርጊቶች

- የስኳር በሽታ ታማሚወች ሽርሽር በሚሄዱበት ጊዜ የሚያስፈልጋቸውን ቁሳቁሶች ማሟላት።
- የስኳር በሽታ ታማሚወችን መርዳትና መደገፍ
- በምግብና በፈተና ጊዜ የበለጠና በቂ ጊዜ መስጠት።

የዋና ስራ አስኪሃጅ ግፀታዊ ዝርዝሮች

የትመህርት ሚንስቴር ዋና ስራ አስኪሃጅ http://bit.ly/1OmDc3e
የጤና ምርመራ የዋና ስራ አስኪሃጅ http://bit.ly/1PpYzE0

## የህክምና ረዳቶች፡

የስኳር በሽታ የጀመራቸው ወጣቶች ከምርመራውና የኢንሱሊን ህክምና ካደረጉ በኋላ ወደ ተማሩበት ትምህርት ቤት የመለሳሉ። በማህበራችን ጥረት በቅርብ ዓመታት ወዲህ እስከ 9 ዓመት ደጋፊ ሰራተኛወች እንዲሰጡ ተወስኗል።
በተለያዩ ጉዳዮችም ከ 9 ዓመት በኋላ የደጋፊ ሰራተኛ ለመቀብል መጠየቅ ይቻላል። የደጋፊ ሰራተኞች የስራ ሥዓት እንዲበዛ ጥረት ስለምናደርግ በድረ ገፃችን መከታተል ይቻላል።

## ልዩ የትምህርት አባል፡

ልዩ የትምህርት አባል እርዳታ የሚሰጠው ከተለያዩ ግምገማወች በኋላ ሲሁን የእርዳታ ጥያቄውን መቅረብ የሚቻለው ታማሚወች በሚያስፈልጋቸውና በሚማሩበት ትምህርት ቤት አስተያየት ሲሆን ከልዩ የትምህርት ማዕቀፎች መመዝገብ ይኖርባቹሃል። http://bit.ly/1U7qoCK.

## ለህፃኖች

ከ 3 ወር እስከ 3 ዓመት ለሆኑ የስኳር በሽታ ታማሚ መዋለ ህፃናት ለሚማሩ ህፃኖች የህክምና ደጋፊ ሰራተኛ መቀበል መብት አላቸው። ይህን እርዳታ ለመቀበል በአካባቢያቹህ ባሉት ማሕበራዊ አገልግሎት መስሪያ ቤቶች ማመልከት ይኖርባቹሃል። ከዚህም በመቀጠል ለማሕበራችን በመደወል ወይም ከድረ ገፃችን በመግባት ይህን እርዳታ ለመቀበል መብታቹህን ማረጋገጥ ትችላላቹህ።

## ከ 3-9 ዓመት ልጆች የደጋፊ ሰራተኛ መቀበል ሂደት

በአካባቢያቹህ ባለው የትምህርት ባለሥልጣን በመሄድ ዶክተሩ መፈረም ያለበትንና ለመሙላት የሚያስፈልጉትን ፋይሎች መቀበል ትችላላቹህ።

በስኳር በሽታ ህክምና ቤት ምሕበራዊ ሰራተኛ እጅ ዶክሜንቱንና ማስረጃዉን በማስሞላት ማቅረብ ይኖርባቹሃል።

ልጆች ስንት ስዓቶች በትምህርት ደረጃ እንደሚውልና የበሽታውን ማስፋፋት ደረጃ መብራራት አሳሳቢ ነው። ከጥቂት ሳምንታት በኋላ የአካባቢ ባለሥልጣን መልስ የሰጣል።

የአካባቢ ባለሥልጣን ከቤተሰቦች ጋር በመተባበር ደጋፊ ሰራተኛ ማገኘት ሃላፊነት አለዉ።

ደጋፊ ሰራተኛ ለመቀበል ጥያቄው ማቅረብ የሚቻለው በተወሰኑ ወራቶች ስለሆነ በትምህርት ባለስልጣን ድረ ገፅ በመግባት መከታተል ይቻላል። አዲስ የስኳር በሽታ ታማሚወች ግን በፈለጉት ጊዜ ይቻላል።

በኮሚቴው መልስ መሰረት እስከ 2 ሳምንት ድረስ በህክምና ፥ በዶክተሩና በትምህርት ቤት

አስተያየት ማስረጃ የተቃውሞ ቃል ማቅረብ ይቻላል።

ይህ ድርጊት እንዲስፋፋ ማሕበራችን ብዙ ጥረት ስለሚያደርግ የተለያዩ ችግሮችና ካጋጠሚቹህ ብታሳትፉን በአግባቡ ልንረዳቹህ እንችላለን።

## በትምህርት መልክ

• የስኳር በሽታ (ዓይነት 1) ታማሚች በበሽታው ህክምና እና ምርመራ መሰረት ብዙ ጊዜ ትምህርት ቤት ስለማይሄዱና ብዙ ትምህርት ስለሚያልፋቸው ማሕበራችን ምናባዊ ትምህርት ቤት ስላቋቋመ ከ 6-18 ዓመት የሆኑ  ወጣቶች የሚያስልጋቸውን የትምህርት ድጋፍ ያገኛሉ። ለተጨማሪ ማብራሪያ ከድረ ገፃችን www.jdrf.org.il በመግባት ወይም
በስልክ ቁጥር፡ 03-5160171 በመደወል መረዳት ይቻላል።

• ተላላፊ በሽታ ታመው ከ 21 ቀን በላይ ትምህርት ቤት ተቀሩ የትምህርት ሚንስቴር የጥናት ድጋፍ ይሰጣል። ለተጨማሪ ማብራሪያ ከዚህ ድረ ገፅ http://bit.ly/1QPsbOD በመግባት መረዳት ይቻላል።

## ልጆች ወደ ትምህርት ቤት መመለሻ ዋና ማሳሰቢያ

ከትምህርት ቤት ጋር የሚያስፈልጉ አግባብነት ርዕስ ጉዳዮች ዝርዝር

መምህሮች/ አማካሪወች/ አስተዳዳሪወች ጋር የምድብ ዝርዝሮች

የስኳር በሽታ ታማሚው ወላጆች ስለበሽታው መስፋፋትና የልጃቸውን ፀባይ ዝርዝር ለአስተማሪች በደምብ ማስረዳት ይኖርባቸዋል።
ዋና ማሳሰቢይ - ይህን ጉዳይ ወላጆች ለአስተማሪወች ብቻ ሳይሆ ልሁሉም የስራ ባልደረቦች ማስረዳት አለባቸው።

**አስተማሪና የስራ ባልደረቦች** - ከላይ በተጠቀሱት ማስረጃወች መሰረት የስኳር በሽታ ታማሚ ተማሪወችን ከሌሎች ተማሪወች በሁሉም ነገር ባለመለየት ማስተማር የኖርባቸዋል። ሆንም ግን የስኳር በሽታ ታማሚ ተማሪወች በበሽታው አስተያየት የሚያስፈልጋቸውን ማሟላት ግዴታ አለባቸው።

**የልጁ ጓደኞች** - ልጁ ከሚግባባቸውና ከሚመቹት ተማሪወች ጋር በመቀራረብ ስለበሽታውና አደጋ ቢደርስ እንዴት አንደሚረዱት ማሳተፍ ይኖርበታል።

**የትምህርት ቤት አማካሪ** - የትምህርት ቤት አማካሪዋ ለልጁ በውስጣዊ ስሜት ብቁ አርዳታ መስጠት ስለምትችል በሁሉም ውሳኔ እሷን ማሳተፍ አስፈላጊ ነው።

**ጤናማ አኗኗር ማስተዋወቅ** - ጤናማ የአኗኗር እና የተመጣጠነ ምግብ አስፈላጊነት በተመለከተ አጠቃላይ ለማጉላት ለትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ማቅረብ ይቻላል።
ሽርሽር ፥ የአካል እንቅስቃሴ ወይም ስፖርትና ፓርቲወች የመሳሰሉትን ድርጊቶች በማካሄድ ለስኳር በሽታ ታማሚወች ማስደሰትና ሰውነታቸውን ያፍታታላቸዋል።

ከቤተሰብ ጋር ግንኙነት - የስኳር በሽታ ታማሚወች ከቤተሰቦቻቸው ጋር በፈለጉት ጊዜ

በስልክ መገናኘት ይችላሉ።

የስኳር በሽታ ታማሚወች ሽርሽር በሚሄዱበት ጊዜ በቂ የሆኑ የህክምና መሰሪያወች መዉሰድ ይኖርባቸዋል።

## ማሕበራዊና ስሜታዊ ገፅታወች

አንዳንዶች ልጆች ሊያፍሩ ስለሚችሉ የሚግባቧቸውና ጓደኞቻቸውን ለራሳቸው እንዲመርጡ ያስፈልጋል።

የስኳር በሽታ ታማሚወች ከመዋለ ህፃናት ወደ ትምህርት ቤት ሲሸጋገሩ የማደግና ጉርምስና ስሜት ስለሚሰማቸው በብልሃትና በትግስት መከታተል ያስፈልጋል።

ብዙ የስኳር በሽታ ታማሚወች ከአንድ ትምህርት ቤት ቢማሩም እያንዳዳቸው ከቤተሰቦቻቸው

| | |
|---|---|
| የጤና መግለጫ ቅፅ | ✔ |
| የሃኪም ቤት ዋና መመሪያና ማስረጃ | ✔ |
| ወላጆች ከደጋፊ ሰራተኛዋ ጋር መገናኘት | ✔ |
| ለአስተማሪወች ትክክል መመሪያ መስጠት | ✔ |
| ለድንገተኛ ሁኔት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች | ✔ |
| ዋና አስፈላጊ ስልክ ቁጥሮች | ✔ |
| ለተማሪወች በሙሉ መመሪያ መስጠት | ✔ |
| የመካሪ ክትትል ማድረግ | ✔ |
| ለሽርሽር በደምብ መዘጋጀት | ✔ |

ጋር የበሽታው አያያዝና ህክምና ልዩ ናቸው። ስለዚህ ወላጆች የልጃቸውን ፍላጎትና ርዕሰ ጉዳይ ለአስተማሪወች በትክክል ማስረዳ ይኖባቸዋል።

## የህክምና ረዳቶችን በተመለከተ አሳሳቢ ማስረጃወች

የህክምና እረዳቶች ልጁ ከሚታከምበት ሃኪም ቤት በመሄድ ስለበሽታው መረዳት ያስፈልጋቸዋል። ከዚህም በመቀጠል ይህን ስራ ለመስራት የሃኪም ቤት ፍቃድ መቀበል ይኖርባቸዋል።

የህክምና እረዳቶች ከአካባቢ ባለስልጣን ተቀጥረው ትምህርት ቤት ስለሚሰሩ የትምህርት ቤቱን ህግጋትና የወላጆችን መመሪያ መጠበቅ ይኖርባቸዋል። ስለዚህ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት የህክምና እረዳቶች ፥ አስተማሪወችና ወላጆች በመሰባሰብ የሚጠበቁ ትብብራትና መመሪያወች መመስረት ይኖርባቸዋል። ከዚህም በመቀጠል የህክምና እረዳቶች ከሃኪም ቤቱ የብለጠ ስለበሽታው መማርና መረዳት ይኖርባቸዋል። ለወደፊቱ የህክምና እረዳቶች በለሉበት ጊዜና ቅያሪ ከለለ ስለሌላ መፍትሄ ማሰብ ይኖርባቸዋል።

**የህክምና እረዳቶች የሚፈቀደው እስከ 9 ዓመት በተለያዩ ሁኔታወች እስከ 10 ዓመት ነው።

## የስኳር በሽታ ታማሚወችን በተመለከተ የሚጠበቁ የትብብር ሂደት ዝርዝሮች

የስኳር በሽታ ታማሚወች መዋለ ህፃናት ፥ ትምህርት ቤትና ወዘተ... በመሳሰሉ ቦታወች የተመቻቸና የሚያዝናና ኑሮ ሊኖሩ የሚያስችሉት ቁልፎች በወላጆችና አስተማሪወች መካከል መደማመጥ ፥ ትብብርና ግልፅነት ናቸው። ምክያቱም የተለያዩ አጋታሚወች ቢደርሱ በትብብር ነው የስኳር በሽታ ታማሚወችን ልጆች መርዳት የሚቻለው። ከዚህም በመቀጥል አንዳንድ አጋጥሚወች ቢደርሱ በአስቸኳይ ማሳወቅ አስፈላጊ ነው።

ሪፖርቶች - በምን ዓይነት አጋጣሚ የስኳር በሽታ ታማሚወች ቤተሰቦቻቸውን ሪፖርት ማድረግ እንደሚችሉ ማሳወቅ አስፈላጊ ነው። እንዲሁም ስለሚፈጠሩ ድርጊቶች በሙሉ የህክምና እረዳቶች ለቤተሰብ ማሳወቅ አለባቸው።

አጋጣሚወችና አስተያየቶች - ሊደርሱ የሚችሉት ድርጊቶች በማሰላሰል ለሁሉም መፍትሄ እንዲኖራቸው ማቀድ አስፈላጊ ነው።

ግንኙነት - በተወሰነ ጊዜ የስኳር በሽታ ታማሚ ወላጆች ፥ አስተማሪወችና የህክምና እረዳቶች ተገናኝተው መወያየት ይኖርባቸዋል።

## የመኪና መንጃ ፍቃድ

የስኳር በሽታ ታማሚወች (ዓይነት 1) የመኪና መንጃ ፈቃድ መውጣት እንዲችሉ ድርጊታችን በማስፋፋት ላይ ነው።

ከስኳር በሽታ ብሔራዊ ምክር ቤት ጋር የሥነ ስርዓቱን ደምብ ለማሳጠር

የትራንስፖርት ሚኒስቴር ዳሪክተር ፊት ለፊት ተጨማሪ ዝውውር ቅጾችን እና በቢሮክራሲ ሂደት የመጀመሪያ ደረጃ ሥር በመጠበቅ ጊዜ በማሳጠር ላይ ነው።

## የህጉ ትእዛዝ ምንድን ነው?

በእስራኤል ሀገር ህግ መሰረት የስኳር በሽታ ታማሚወች የመኪና ፥ ሞተር ሳይክልና የጭነት መኪና መንጃ ፍቃድ ማውጣት ይችላሉ ፤ ከዚህም በመቀጠል ታክሲ ፥ አምቡላንስ ፥ አይሮፕላንና ከ 3 ቶን በላይ የሆኑ ተሽከርካሪወች መንዳት አይችሉም።

የመኪና መንጃ ፈቃድ መውጣት የሚፈልጉ ብሔራዊ ትራፊክ ደህንነት ተቋም ሚኒስቴር የፈቃድ ማረጋገጫ ፍቃድ ሳይቃበሉ ምንም ሂደት መጀመር የለባቸውም።

## ለሂደቱ ምን አይነት ተያያዥነት አለው?

አሁን በአለው አያያዝ መሰረት ይሚሞሉ 2 ልዩ ቅርጾች አሉ

1. በጠበቃ ወይም ፍርድ ቤት ፊት የህመሙን ማብራሪያ ማስረጃ ማቅረብ
http://bit.ly/20GpGhH

2. ለስኳር በሽታ መርማሪው ዶክተር የሚሞሉ ዶክሜንቶ ወይም ቅርፆች ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

የሚያስፈልጉት ዶክሜንቶች በሙሉ ከድረ ገፃችን አሉ።

www.jdrf.org.il

ግዜን በአግባቡ ለመጠቀም ቅፆችን በመሙላት ከአረንጓዴው ዶክሜንት ጋር በማያያዝ ዲኤምቪ ብታቀርቧቸው ይመረጣል።
በጭማሪ እኒህን ዶክሜንቶች አባዝታቹህ ለራሳቹህ ብታስቀሩ ለእናንተ ይረዷቹሃል።

ከዚህ በመቀጠል ዲኤምቪው ቅፆችን ወደ ብሔራዊ ትራፊክ ደህንነት ተቋም ሚኒስቴር ለምርመራ ያሳልፋቸዋል ፥ ምርመራውም በክፍያ ስለ ሆ ነ ያልከፈሉ ሰወች ቅፆቻቸው አይመረመሩም።
ክፍያውን (118 ብር) በመንግስት የድር ጣቢያ ክፍያ መክፈል ይቻላል። bit.ly/1Mkp2yB

የመንገድ ደህንነት ተቋም በጥንቃቄ ቅፆችን ስለሚመረምራቸው በደምብ ተስተካክለው ቢሞሉ ይመረጣል።
ምርመራው 1 ወር ከፈጀ በኋላ መልሱ ወደ ዲኤምቪው ስለሚላክ ሄዳቹህ መቀበል ትችላላቹህ።

JDRF IMPROVING LIVES. CURING TYPE 1 DIABETES.
האגודה לסוכרת נעורים (סוג 1) בישראל

በተጨማሪም የመኪና መንጃ ፍቃድ ያለው የስኳር በሽታ ታማሚ በመኪናው የምርመራ መሳሪያወች መያዝ ይኖርበታል።

1. ዲኤምቪና በሔራዊ ትኩረት ስ.ቅ፡ 8765-222-1 ወይም *5678
2. የመንገድ ደህንነት ተቋም አድራሻ፡ ዴሬህ በጊን 116, ቴል አቪቭ ከተማ
 ስ.ቁ፡ 03-5634702 ፋክስ: 03-5626022

## የውትድርና እና ብሕራዊ አገግሎት

ከ 16 ዓመት ወደ መጀመሪያ ምዝገባው ትዕዛዝ እና የመጀመሪያ የማጣሪያ ምርመራ መርሐግብር ወደ እናንተ ይላካል። በዚህ ጊዜ እያንዳንዱ የጤንነት ማስረጃ ፋይል ማመጣት ባለበት መሰረት የስኳር በሽታ ታማሚወችም ከውትድርና አገልግሎት ነፃ ለመሆን ስለበሽታው የህክምና ማስረጃ ወረቀት ማምጣት ይኖርባቹሃል።

ይህን መግለጫ ውሳኔ ለማፋጠን የሀኪም ምርመራ ዝርዝርና የሚያስፈልጉት ዶክሜንቶች በትክክል አሚልቶ መውሰድ ይኖርባቹሃል። http://bit.ly/1MBI5Ep

በፍቃደኝነት ውትድርና ሙሉ ወይም ግማሽ ጊዜ ለማገልገል የሚፈልጉ ደግሞ ካዛው ቦታ መጥቀስ ይችላሉ።

በፍቃደኝነት ውትድርና ማገልገል ለሚፈልጉ እስከ 21 ዓመት መዘግየት ይቻላል።

በፍቃደኝነት ለሚፈልጉት ወታደሮች ትርጉምና ጠቀሜታ ያለው አገልግሎት እንዲኖራቸው ማህበሩ ትልቅ እጥረት እያረገ ይገኛል።

ከዚህም በመቀጠል እኒህ ወታደሮች ምቾታማና እሚያረካ የውትድርና ጊዜ እንዲያገለግሉ ሮቴም ከሚባለው ኢንዱስትሪ ጋር በመሆን እንጥራለን።

በመህበሩ ጥረት ከ 2003 ዓ.ም ጀምሮ የስኳር በሽታ ታማሚ ወጣቶች በፍላጎታቸው ውትድርና የሚያገለግሉት ቁጥራቸው በበዙ ተስፋፍቷል። ውትድርና ከጨረሱ በኋላም እንደ ሁሉም ወታደሮች የገንዘብ እርዳታ ይሰጣሉ።

## ውትድርና ለመሄድ የሚደረጉ ሂደት ደረጃወች

ውትድርና ለማገልገል ፍላጎታቹህን ከገለፃቹህ በኋላ የሚቆጠሩ የምልመላ ሂደቶ አሉ።
የግል ውሂብ ማረጋገጫ ፥ የፕሲሆሜትሪክ ፈተና እና የህክምና ኮሚቴ ምርመራ ይደረጋል።
የህክምና ኮሚቴው የቀረቡትን መረጃወች ከመረመረ በኋላ በሽታው ውትድርና ለማገልገል ካስቻለና ዉጤቱ HbA1c< 9 ከሆነ ፍቃድ ይሰጣሉ።
ከወትድርና ማገልገያ ቦታ (ባሲስ) ለማደርና ለምሰንበት የሚፈልጉ ወታድሮች የበለጠ ምርመራ ማድረግ ይገደዳሉ።

ውትድርና ለማገለገል ፍቃድ ለመቀበል ሂደቱ ብዙ ጊዜ ስለሚወስድ አስቀድሞ መጀመር ያስፈልጋል።
በማህበሩ እጥረትና እርዳታ መሰረት የተለያዩ ሞያወች እየተስፋፉ ስለሄዱ የምትፈልጉትን በደንብ መርምራቹህ በመምረጥ ማገልገል ትችላላቹህ። ውትድርና ከመግባታቹህ በፊት ኩርስ የሚያስፈልጉ አዳዲስ የሚመቹ ሞያወችም ስላሉ የህን ይመስላሉ
የስልጠና ሚና ፥ የውጊያ ደጋፊ ፥ የስለላ ተግባሮች ወዘተ...
እንዲሁም በዓመት 1 ቀን በኅዳር ወር እድሚያቸው ለውትድርና መገልገል ለደረሱት ወጣቶች የስብሰባ ጉባኤ እናደርጋለን።

## ውትድርና በሚሄዱበት ቀን ምን ይደረጋል?

ውትድርና በምተሄዱበት ቀን ጧት በመነሳት በአካባቢያቹህ ባለው የወታደር ምልመላ አድራሻ ከሄዳቹህ በኋላ ኦቶቡስ ከድርደራ መቀበያ ቦታው የዟቹህ ይሄዳል። ከዛም አጭር የስም ዝርዝር ማረጋገጫ ከተደርገ በኋላ የክትባት መርፌ ተወግታቹህና ፎቶ ተነስታቹህ የውትድርና ልብስ ትቀበላላቹህ። አብዛኛውን ጊዜ በፍቃዳቸው የውትድርና አገልግዮች ቦታ

ካምፕ የሚያደርጉበት “ባድ 7” በተባለ ቦታ ነው።

## በውትድርና የህክምና አገልግሎት

የህክምና አገልገሎት የምትሰጡት እስከዛሬ ስትታከሙበት ከነበረው ሃኪም ቤት ነው ፤ ምክኒያቱም እስከዛሬ የነበረው የሃኪም ቤቱ ቁጥጥር እንዳያቋርጥና ህክምናውን በአግባቡ እንድትቀጥሉ ነው።
በውትድርና አገልግሎት መካከል ብትቆስሉና ሌላ በሽታ ቢዛቹህ ተጨማሪ የጤና መድን (ቢቱህ) መግዛት ትችላላቹህ። የህን የጤና መድን ያለው የህክምና አገልግሎትና ከኒና በነፃ መግዛት ይችላል ፤ በእራሱ ገንዘብ የገዛም ይመለስለታል። ከዚህም በመቀጠል በተገቢው እንደሌሎች ሁሉ የክትባት መርፌ መከተብ ያለባቹህን ክትባት በነፃ መከተብና እንዲሁም የጥርስ ህክምና ወይም መነፀር መቀበል ይቻላል።

### ማሳሳቢያ

የውትድርና ማገልገል ፍቃድ ከተቀበላቹህ በኋላ የስኳር በሽታ ምርመራ ዝርዝር ማስረከብ ግዴታ ነው። ከሚያስፈልገው የበለጠ ውትድርና ማገልገል የሚፈልጉ የስኳር በሽታ ምርመራ ክትትሉ ወደ ጦር ሰራዊት ይተላለፋል።

## የውትድርና አገልጋዮች መብት

የሚያድሩና የሚሰነብቱ ወታደሮች መብታቸው ከሌሎች ወታደሮች ጋር አንድ ነው። ከዚህ አልፎ መሳሪያ የመያዝ መብት ቢኖራቸውም መጠበቅ አያችሉም ፥ በሚያገለግሉት ጊዜም ለሃላነት ኩርስ ለመውጣት ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ።

በሚከተሉት መንገዶች ሕዋስ የእውቂያ:

ስ.ቁ፡ 03-7487157

እሁድ - ሀሙስ ከ 08፡00-12:00 13:00-17:00

ፋክስ፡ 03-7487207 ስልክ በመደወል መድረሱን መረጋገጥ ይኖችባቹሃል።

ኢሜል - tash@idf.gov.il

እነዚህ መብታቹህ ከተጣሱ ለእኛና ለሎችችም አባላቶች ማመልከት ትችላላቹህ።

<u>የግል ጉዳት ማመልከቻ</u>

ለህዝብ ጉዳይ ሃላፊዋ በስ.ቅ፡ 03-5691000

ወይም በፋክስ 03-5699400 ማመልክት ይቻላል።

<u>የህክምና ጉዳት ማመልከቻ</u>

ለዋና የህክምና ሃላፊ በስ.ቁ፡ 03-9489999 ማዞሪያ 3 ደውሎ ማመልከት ይቻላል።

## ብሄራዊ አገልግሎት (ሼሩት ለኡሙሚ)

ውትድርና ማገልገል የማይችሉ የስኳር በሽታ ታማሚወች ወጣቶች ብሄራዊ አገግሎት በመስጠት የተለያዩ መብቶች ማገኘት ይችላሉ።

በእምነት ወይም ሌላ ምክንያቶች ውትድርና ማገልገል የማይችሉ ወንድና ሴቶችም እንዲሁ ብሄራዊ ፥ በትምህርት ፥ ቤቶች በህክምና ክሊኒኮች ፥በህፃናት ማሳደጊያና አዲስ ገቢ መናህሪወች ማገልገል ይችላሉ።

## ብሄራዊ አገልግሎት ለመስጠትና ለመመዝገብ ከሚከተሉት ድርጅቶች ማመልከት ይቻላል።

የሽሎሚት ድርጅት ስ.ቁ፡ 03-612922
ድረ ገፅ - www.shlomit.org.il

የበጎ አድራጊ ማሕበር ስ.ቁ፡02-6521140
ድረ ገፅ - www.sherut-leumi.co.il

ቤት ዓሚ ድርጅት ስ.ቁ፡ 02-6443333
ድረ ገፅ - www.bat-ami.org.il

## ውጭ ሀገር ጉዞ

ለጉብኝት ውይም ለስራ ወደ ውጭ ሀገር አሚበሩ ሰወች ከመሰፈሪያ ከትኬቱ ውጭ የህክምና

ምርመራና በሚያደርጉበት መሰረት ይስኳር በሽታ ታማሚወችም የበለጠ ምርመራ ማድረግ አለባቸው።

ውጭ ሀገር ለሚበሩ በትቂቱ ምክሮች

## ከመብረራቹህ በፊት

ውጭ ሀገር ለመብረር ስትፈልጉ ከብዙ ጊዜ በፊት ከስኳር በሽታ ሃካሚው ዶክተር ወረፋ መያዝ ይኖርባቹሃል። ምክንታቱም የሚያስፈላቹህን ነገሮ በደምብ ለማዘጋጀትና የህክምና ውጤቱን በጊዜ እንድትቀበሉ ነው።
ከመብረራቹህ በፊት ከሃኪም ቤት የፍቃድና የስኳር በሽታ ታማሚ (ዓይነት 1) እንደሆናቹህና ምርመራውን እንደምትከታተሉ ማስረጃ ወረቀት መቀበል ይኖርባቹሃል። ልምተዱባት ሀገር ማስረጃ ወረቀቱን በንግሊዘኛ መተርጎም ይኖሩባቹሃል። ድረ ገፅ www.jdrf.org.il ለያልታሰበ አጋጣሚ መተማመኛ ግሉካጎ መያዝ ያስፈልጋል።
ከዚህም ከጓደኞቻቹህ የምትበሩ ከሆነም የመርፌው አጠቃቀም ብትነግሯቸው ሊረዷቹህ ይችላሉ። የምትሄዱባት ሀገር ስዓትና ወራት ልዩ ከሆነ የከኒንና መርፌ በደምብ መከታተል ይኖርባቹሃል ፤ ይህን ማስረጃ ደኩተሩ ሊገልፅላቹህ ይችላል።
ወደ ውጭ ሀገት ለመሄድ ስትፈልጉ ከ 3 ወር በፊት ከኒኖችንና መርፈውችን ማዘጋጀት ይኒርባቹሃል። አብረዋቹህ የሚጓዙ ጓደኞች ወይም ቤተሰቦች ካሉ ለእነሱ አጠቃቀሙን ትስረዷቸው። ከኒኑና መርፌው ካለቀባቹህ ባላቹህ የሚያስፈጋቹህን ለመግዛት ይህክምና ማስረጃ ወረቀት ይዛቹህ መዞር አለባቹህ

## ማሳሰቢያ

በአየር ፀባይና በሰውነት እንቅስቃሴ በሽታው ሊስፋፋና ሊጠነክር ስለሚችል በብዛ ግሉኮስና የኢንሱሊን መርፌ መያዝ ያስፈልጋል። የምተዱበት ቦታ ንፅህና ባይኖረውም በመርፌ

ስትጠቅሙ ሰውነታቹህ ንፁህ መሆን አለበት።

## የህክምና ማገልገያ እቃወች

የህክምና እቃወችን በፓጋዙ ሳይሆን በትንሽ ሻንጣ ከምትቀመጡበት ቦታ አብሮ መጓዝ አለበት።
ከማታዉቁት ቦታ ከኒኑንና የህክምና እቃወችን አትግዙ።
በትሄዱበት ሆቴል ባለው ፍሪጅ ማኖረለባቹህ።
መግዣ ቦታ ከታጣ ደግሞ ከዚህ ሀገር በፖስት መላክ ስለሚችል ሂደቱንና እንዴት መላክ እንደሚቻል ማረጋገጥ ይኖርባቹሃል።
ወደ ውጭ ሀገር ከመሄዳቹህ በፊት የምትወስዷቸው የህክምና እቃወች መስራታቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው።
የኢንሱሊን መድሃኒ ፀሃይ እንዳይደርስበት በልብስ ጠቅልሎ ማኖር ያስፈልጋል።
ቀዝቃዛ ቦታወች የምትተኙ ከሆነ በረዶ እንዳይሆን ከቦርሳቹህ ወይም ለብሳቹ ከምተኙት ውስጥ ማኖር ይኖርባቹሃል።

JDRF

IMPROVING LIVES. CURING TYPE 1 DIABETES.

በዚህ መፅሄት የቀረቡት ማስረጃወች በሰፊዉ መብራሪያ በመሆናቸው ህጋዊ ምክርና የመሳሰሉትን አገልግሎት አይሰጡም። ከዚህ በመቀጠል የመፅሄቱ የተዘረዘሩት መስረጃወች በህጋዊ ደንብ ቢቀርአቡም ማስረጃወችን በተመለከተ ፍርድ ቤት  ወዘተ... ለመሳሰሉት ቦታወች ተማምኖ ለማቅረብ አይቻልም ፤ምክንያቱም በመፅሄቱ ማስረጃና በህግ ፍርድ ቤት ቅራኔ ከኖረ የህግዊ ፍርድ ቤት ማስረጃ ስለሚበልጥ ንው።

የመፅሄቱ ማስረጃወጅ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሳሉና እየታረሙ በማህበራዊ ድረ ገፅ ይሰራጫሉ።

בתמיכת:

Medtronic Further, Together

novo nordisk®

Lilly | DIABETES

SANOFI DIABETES